# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

**የዓቢይ ጾም ስድስተኛ ሰንበት «ገብርኄር» ይባላል።**

ስያሜው የቅዱስ ያሬድ ሲሆን በዚህ ቀን ስለ ቅን አገልጋዮች፣ ለአገልጋዮች የሚያገለግሉበትን ጸጋ የሚሰጥ ወኃባ ጸጋ አገልጋዮቹን «ገብርኄር» እያለ ዋጋ የሚሰጥ አምላክ መሆኑ እየታሰበ ይመለካል።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

መኑ ውእቱ ገብርኄር
ቸር አገልጋይ ማነው?

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፪ኛ ጢሞ ፪፥፩-፲፮ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፭፥፩-፲፪ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፩፥፮-፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ምስባክ

ከመ እግበር ፈቃድከ መከርኩ አምላኪየ
ወሕግከኒ በማእከለ ከርስየ
ዜኖኩ ጽድቅከ በማኅበር ዐቢይ

አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድኩ
ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው
በታላቁ ጉባኤም ጽድቅህን አወራለሁ (ተናገርኩ)

መዝ ፴፱፥፰

ትርጉም፥
አቤቱ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን (ሕግህን ወንጌልህን) እናገር ዘንድ ወደድኩ። ሕግህ በልቦናዬ ተጽፎ ይኖራል፣ ቸርነትህንም በብዙ ጉባዔ ነገርሁ።

**ወንጌል፥** ማቴ ፳፭፥፲፬-፴፩
**ቅዳሴ፥** የባስልዮስ

## የዕለቱ ትምህርት

### ቸር አገልጋይ ማነው?

ቸር አገልጋይ (ገብርኄር) ማቴ ፳፭፥፲፬-፴ በዚህ ዕለት በቅዳሴ ሰዓት የተነበበው ቃለ ወንጌል እንዳመለከተን መድኃኒታችን የወንጌልን አደራ በምሳሌ እንዳስተማረ ተገንዝበናል። ትምህርቱም አንድ ባለጸጋ ሰው ነበር። ወደ ሩቅ አገር ለመሄድ ባሰበ ጊዜ አገልጋዮቹን ጠርቶ ለመንገዱ እስኪመለስ ድረስ ይሰራበት ዘንድ ለአንዱ አምስት መክሊት፣ ለሁለተኛው ሁለት፣ ለሦስተኛው አንድ መክሊት (ታለንት) ሰጣቸው። አምስት መክሊት የተቀበለው ወጥቶ ወርዶ ሌላ አምስት መክሊት በማትረፍ አሥር መክሊት አደረገው። ሁለት መክሊት የተቀበለውም ወጥቶ ወርዶ እጥፍ አትርፎ አራት መክሊት አደረገው። አንድ መክሊት የተቀበለው ግን ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት በልቡ ውስጥ ስጋት፣ ጥርጥርን፣ ፍርሃትንና አለማመንን ስላነገሠ ስሰራበት ቢጠፉብኝስ? ቢሰርቁኝስ? ቢቀሙኝስ? እያለ በማሰብ እሰራለሁ ብዬ ያለኝን ከማጣ ለምን ደብቄ አስቀምጬ በመቆየት ሲመጣ የሰጠኝን አልመልስም ብሎ መክሊቱን ቆፍሮ ቀበረው። ጊዜው ሲደርስ ባለንብረቱ መጣና አገልጋዮቹን ይተሳሰባቸው ጀመር።

በቅድሚያ፥ አምስት የወሰደው መጣና «ጌታዬ ሆይ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር። ይኸውና ሌላ አምስት መክሊት አትርፌአለሁ» ብሎ አሥር መክሊት ለጌታው ሰጠ። ጌታውም «መልካም አደረግህ፤ አንተ መልካም አገልጋይ (ገብርኄር) በጥቂቱ ስለታመንህ በብዙ ላይ ስለምሾምህ ና ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» አለው።

ሁለተኛው፣ «ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር። እነሆ አራት መክሊት» ብሎ እጥፍ ማትረፉን ገልጾ ለጌታው አስረከበ። እንደባለ አምስቱ «መልካም አደረግህ ቸር አገልጋይ ነህ በጥቂቱ ስለታመንህ በብዙ ላይ እሾምሃለሁ» ተባለ።

ሦስተኛው፥ መጣ ሰነፍ ቃሉም መራራ ነው። የሰነፍ አካሉ ብቻ ሳይሆን አእምሮውም ሰነፍ ነው። ጌታው ገንዘቡን ሲጠይቀው፥ «ጌታ ሆይ፥ አንተ ካልዘራህበት የምታጭድ፣ ካልበተንክበትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ። ስለዚህ ፈራሁህ ሄጄም መሬት ቆፍሬ መክሊቴን ጉድጓድ ውስጥ ቀበርኩት። ገንዘብህ ይኸውልህ ውሰድ አለው። ጌታውም ይህን ያህል ጨካኝ እንደሆንኩ ካወቅህ ንብረቴን ከነወለዱ ልትመልሰው ይገባህ ነበር። ገንዘቤን ልትሰራበት ሲገባህ ለምን ቀበርከው ብሎ መክሊቱን ወደ እርሱ ወስዶ ለባለ አምስቱ ጨምሩለት «ላለው ይጨመርለታል ይትረፈርፍለትማል፤ ለሌለው ግን ያው ያለው ይወሰድበታል» ይህንን የማይረባ አገልጋይ ግን ልቅሶ፣ ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ጽኑ የፍርድ ቦታ ውሰዱት አለ ይላል በምሳሌ የተሰጠው የመድኃኒታችን ትምህርት። የትምህርቱም ትርጉም እንደሚከተለው ነው።

የንብረቱ ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሦስቱ አገልጋዮች ልዩ ልዩ ጸጋ ተሰጥቶአቸው ያሉ ሕዝበ ክርስቲያኖች ምሳሌዎች ናቸው። ስጦታው በአኃዝ ሲታይ ልዩነት መኖሩ አንዱ ጸጋ ከሌላው የሚለይ መሆኑን ያሳያል።

### የአገልጋዮቹ ባሕርይ

፩) የመጀመሪያውና የሁለተኛው አገልጋዮች መንፈስ ሁለቱም ሠርቶ ማግኘት እንደሚቻል የሚያምኑ፣ ለጌታቸው ታማኞች፣ በሥራ ላይ የሚያጋጥማቸውን ችግር በማሰብ ጊዜአቸውን የማያጠፉ ናቸው። ሁለተኛው አገልጋይም እንደ መጀመሪያው አገልጋይ ለምን አምስት አልተሰጠኝም ብሎ ያለኩርፊያ በተሰጠው የሚሰራ ነው። ባለአምስቱ አምስት ሲያተርፍ ባለሁለቱም ሁለት በማትረፍ ተመሳሳይ ትጋት የታየባቸው አገልጋዮች ናቸው። ዋጋቸውንም እኩል ነው ያገኙት። ለሁለቱም የተሰጠው የክብር ስም አንድ ነው። ገብርኄር (ቸር አገልጋይ) የሚል የገቡበትም የክብር ሥፍራ አንድ ነው። ያም «የጌታችን ደስታ» ነው። ሁለቱም በጥቂቱ የታመኑ ነበሩ። ከሰጪው አንጻር ሲታይ የባለ አምስቱም እንደ ባለ ሁለቱም፤ የባለሁለቱም እንደ ባለአምስቱ ጥቂት ነበር። ሰው በተሰጠው ሳያንጐራጉር ፈጣሪውን ቢያገለግል ክብር ያገኛል። ለሰው ልጅ የሚጠቅመው ችሎታውን፣ ጸጋውን መቁጠር ሳይሆን በተሰጠው ጸጋ ማገልገል ነው። እነዚህ አገልጋዮች በእውነት በፍቅር በእምነት የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ያመለክታሉ።

፪) የሦስተኛው አገልጋይ ባሕርይ፥ መልካም ጐኑ ስጦታው አነሰኝ አለማለቱ ነው። በርግጥ ስንፍናውን ስለሚያውቅ ይሆናል። ይህ ሰው ከሥራ ይልቅ በሥራ ጊዜ የሚፈጠረው ችግር አስቀድሞ ይታየዋል (የሰነፍ አርቆ አስተዋይ) ሲያተርፍ ሳይሆን ሲያተርፍ ብቻ ይታየዋል። አንዱን ሁለት ሲያደርግ ሳይሆን ያንኑ ያለውን ሲቀማ ይታየዋል። በጌታው

ፊት እንደወንድሞቹ ዓይነቱን ትርፍ ይዞ ቀርቦ ሲሸለም ሳይሆን ዓይነታውም ጠፍቶበት ለጌታው የሚመልሰውን ሲያጣ ይታየዋል። በመሆኑም ምንም መስራት አልቻለም። የተሰጠውን መክሊት ኪሱን አላምነው ብሎ መሬት ቆፍሮ ቀበረው። በአጠቃላይ ባለማመን የተያዘ ሰው ነው። ከጌታው ፊትም ሲቀርብ በጐ አገልጋዮቹ ያልተናገሩትን ነው የተናገረው። «ጨካኝ መሆንህን ስላወቅሁ ይጠፋብኛል ብዬ ብርህን አስቀምጨልሃለሁ፤ ይኸውልህ ና ውሰድ» ነው ያለው። ሰነፍ የሚናገረውም አያምር ተቀምጦም መፀት ከማውራት ዝም አይልም።

ዛሬም ቢሆን ተቀምጠው መፀት የሚያወሩ የእግዚአብሔርን ጸጋ የቀበሩ፤ ባስተምርና መናፍቅ ተከራክሮ ቢረታኝስ? የማውቀውን እውነት ለመስበክ ስጀምር ቢያሳስሩኝስ? በቤተ ክርስቲያን በሕዝብ በገበያ በልዩ ልዩ ቦታዎች ያሉትን ኃጢአተኞች ብቃወም ጠላት ሆነው ቢነሱብኝስ? ለምን ዝም ብዬ ደመወዜን ሳልሰራ አልበላም ብለው የሚኖሩ ስንት አገልጋዮች አሉ። የዚህ ሰው ችግሩ መክሊቱ አንድ መሆኑ ሳይሆን በዚያው በተሰጠው አለመስራቱ ነው። የተሰጠውን ጸጋ እያንዳንዱ አምኖ በመቀበል ሊያገለግል ይገባዋል። ባለ ሁለቱ በባለ አምስቱ፣ ባለ አንዱ በባለ ሁለቱ ሊቀና አይገባውም። ሁሉም ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ ቄስ አይሆንም። ሁሉም ግን በተሰጠው ጸጋ ቢያገለግል እውነተኞች ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት የሚያገኙትን ዋጋ ያገኛል። ሁሉም ባለ ራእይ፣ ወንጌላዊ፣ ዘማሪ፣ ፈዋሽ ሊሆን አይችልም። ለእያንዳንዱ ልዩ ልዩ ጸጋ አለው። ሁሉም በጸጋው ቢያገለግል እኩል ዋጋ ያገኛል።

አንባቢ ሆይ፥ በሦስቱ አገልጋዮች አምሳል የተጠቀሱት አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን የሚኖሩ ልዩ ልዩ የጸጋ አገልግሎት ያላቸው ክርስቲያኖችን የሚመለከቱ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ባለ አምስት አገልጋዮች አሉ፤ በወንጌል፣ በእረኝነት፣ በእርዳታ በልዩ ልዩ ጸጋ አንዱን ጌታ በቅንነት የሚያገለግሉ ሰዎች ምሳሌ ናቸው። ባለ ሁለቱም እንዲሁ ልዩ ጸጋ ያለው በጸጋውም የሚያገለግል የጌታ አገልጋይ ምሳሌ ነው። ባለ አንዱ ግን ጸጋ እግዚአብሔርን የተቀበለ ግን በጸጋው የማያገለግል ደካማ ሰው ነው። ምናልባትም ይህ ሰው ራሷ ክርስቶስ በሆነላት ቤተ ክርስቲያን እግር ሆኖ ቢፈጠር ኖሮ የማይሄድ፤ እጅ ቢሆን የማይዳስስ፤ ዓይንም ቢሆን የማያይ … ስንኩል አካል ነው። በመሆኑም የክርስቶስ አካል ሆኖ ለመቀጠል አይችልም።

ወንድሜ አንተስ ጸጋህ ምንድን ነው? ጸጋህን ታውቀዋለህን? ታገለግልበታለህን? መቼም ክርስቲያን ሁሉ የክርስቶስ አካል ነው። የሥራ ድርሻ የሌለው የአካል ክፍል ደግሞ የለም። አንተም/አንቺም የክርስቶስ አካል ነህ/ነሽ። ስለዚህ አካሉ በመሆንህ/ሽ ደግሞ ጸጋ አለህ/አለሽ። በመሆኑም እንደጸጋችን እናገልግል፤ ጸጋውን እንቀበለው፤ ወንጌልን በጊዜውም አለጊዜውም ሲሞላልንም ሲጐድልብንም እንስበክ፤ ሐብታሙ ይመጽውት፤ መምህሩ ያስተምር፤ ዘማሪው ይዘምር፤ ጸሐፊው ይጻፍ፤ ሁሉም በጸጋው ያገልግል። አንድ መክሊት እንደተቀበለው ሰው ነገ እንዲህ ቢሆንስ እንደዚያ ቢፈጠርስ እያልን ባለማመን ዕለታትን ጊዜአትን አናባክን። በመጠራጠር ክፉውን እንጂ በጐውን፤ ጥፋትን እንጂ ትርፍን ባለማሰብ ባለማመን ከአገልግሎት አንቆጠብ። መከራም ቢመጣ ሞትም ቢመጣ በጐም ሆነ ክፉ ነገር ቢከሰት ነገን የሚያውቅ ጌታ ብቻ ነው። ሰው ይጠላኛል፤ ክብሬ ይቀነሳል፤ ስሜ ይጠፋል፤ መናፍቅ ተከራክሮ ይረታኛል፤ ነገ ችግር ይገጥመኛል፤ እሰራለሁ አገለግላለሁ ብዬ ከምሰናከል ከምፈተን ለምን ዝም ብዬ አልቀመጥም አንበል። ለሥራ ለአገልግሎት እንነሳ። እንደ ሁለቱ ቅን አገልጋዮች ይሳካልናል። ቃሉን በእዝነ ሰማእያን እንዝራው ይበቅልልናል። ገበሬ እንኳ «ከወፍ አእላፍ አብላኝ» ብሎ በእምነት የተለቀመውን ዘር (እህሉን) ወደ ጫካ ጥሎ (ዘርቶ) ምን እንደሚያመርት ተፈጥሮ ያስተምረናል። ገበሬው የዘራሁት ባይበቅልስ ወፍ ቢበላውስ ብሎ ቢያስብ ኖሮ ባልዘራም ምርትንም ባላፈሰ ነበር።

ዛሬም እኛ ቅን አገልጋዮችን በእምነት እንምሰላቸው፣ በፍቅር በእምነት እናገልግል ዋጋ እናገኛለን። ልንጨነቅበትና ልንቀብረው የተሰጠን ጸጋ የለምና የምናተርፍበትን እንጂ ኪሳራ የሚሆን ጸጋ አልተሰጠንምናእንደ ሰነፉ አገልጋይ ኪሳራችንን ሳይሆን ትርፋችንን፤ ሞታችንን ሳይሆን ሕይወታችንን፤ ውርደታችንን ሳይሆን ክብራችንን እያሰብን ልናገለግልበት ይገባናል።

ከቅዱስ ያሬድ በቅዳሴ ጊዜ በተነበቡት መጻሕፍት ከትምህርቱ ጋር የሚሄዱ ጥቅሶቹን እንመለከታለን።

ጥቅስ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ «ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ ብዙዎች የመሰከሩትን ከእኔም የሰማከውን … ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑት ሰዎች አደራ ስጥ።» (፪ኛ ጢሞ ፪፤፩-፫)

«የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በግድ ሳይሆን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ … ለትሑታን ጸጋን ይሰጣል» (፩ኛ ጴጥ ፭፤፩-፬)።

«… መንፈስ ቅዱስ በእናንተ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» (የሐዋ ሥራ ፩፤፮-፱)።

ጥቅስ ከቅዱስ ያሬድ መዝሙር

*በግእዝ፥ «መኑ ውእቱ ገብርኄር ወምእመን ዘይረክቦ እግዚኡ በምግባረ ሠናይ ወይሰይሞ ዲበኩሉ ንዋዩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ገብርኄር ወምእመን ዘበውሁድ ምእመነ ኮንከ ባዕ ውስተ ፍስሐሁ ለእግዚእከ»* (መዝሙር)

በአማርኛ፥ በጐ ሥራ እየሠራ ጌታው የሚያገኘው ቸር እና የተመነ አገልጋይ ማነው ባለው ሁሉ ላይ የሚሾመው ደግሞም እግዚአብሔር ቸር ታማኝ አገልጋይ በጥቂቱ የታመንከ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ የሚለው»

*በግእዝ፥ «ኩኑ እንከ ከመአግብርት ኄራን ወከመ አግብርተ ክርስቶስ ምእመናን አለይጸንሐ እግዚኦሙ እስከየአቱ እምከብካብ ዘበሰማያት» (አራራይ)*

በአማርኛ፥ «እንደ ቅን አገልጋዮች፤ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች ምእመን ሁኑ ጌታቸው ከሠርግ እስኪመለስ ድረስ ተግተው እንደ ጠበቁት» (ሉቃ ፲፪ ጋር አነጻጽሩ)።

*ከመ ገብርኄር ለእግዚአብሔር ተቀነዩ በኩሉ ጊዜ ወበኩሉ ሰዓት (አዝ) በኩሉ መአልት ወበኩሉ ሌሊት (አዝ) ጹሙ ወጸልዩ በንጹህ ልብ ወአክብሩ ሰንበተ (አዝ) ለቢጽክሙ ሠናይ ሀልዩ አብ ይሄሊ በእንቲአክሙ (አዝ) ወአግእዝዋ እምኃጢአት ለነፍስክሙ።»*

አማርኛ፥ «እንደ ቸሩ አገልጋይ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ በሰዓቱ ሁሉ በጊዜው ሁሉ በመዓልት በሌሊት፤ በንጹህ ልብ ጹሙ፤ ጸልዩ፤ በእውነት ሰንበትን አክብሩ፤ ለጓደኞቻችሁ በጐ አስቡ፤ አብም ስለ እናንተ ያስባል ከኃጢአት ነፍሳችሁን ነጻ አውጧት» (ዘካ)

እኛም በቅን እንድናገለግለው ጌታ ይርዳን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።